የሰ/መ/ቁ. 48783

ሐምሌ 27 ቀን 2002 ዓ.ም

***ዳኞች፣*** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

***አመልካች፣*** ወ/ሮ ሶፊያ ሁሴን - ጠ/አሉወርቅ ደጀኔ ቀረቡ

***ተጠሪዎች፣*** 1. የአራዳ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር - ነ/ፈጅ ሰሎሞን ተመቸው --ቀረቡ

2. አቶ ገዛኸኝ ሀብቴ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ***ፍ ር ድ***

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የመተላለፊያ መንገድ የማግኘት ጥያቄ አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአመልካች ከሣሽነት ነው የዳኝነት ጥያቄያቸውም የመተላለፊያ መንገድ ስለጠበባቸው ለአስተዳደሩ አመልክተው ከሁለተኛ ተጠሪ 1.10 ሜትር ተቀንሶ መንገድ እንዲያገኙ በአስተዳደሩ ከተወሰነ በኃላ ባልታወቀ ምክንያት አፈፃፀሙ በአንደኛ ተጠሪ ስለታገደ እና ሁለተኛ ተጠሪም የፈረሰውን አጥር መልሶ እያሰራ ስለሆነ ሁከት ተወግዶ በቀድሞ የአስተዳደሩ ውሣኔ መሠረት መንገዱ እንዲከፈት እንዲወሰን የሚል ነው፡፡

አንደኛ ተጠሪ ሥር ፍ/ቤት የሰጠው መልስ የአስተዳደሩ ውሣኔ አፈፃፀም በሁለተኛ ተጠሪ ላይ ከሚያደርስው ጉዳት አንፃር ቴክኒካዊ መፍትሔ በአስተዳደሩ ባለሙያዎች ቀርቦ አመልካች ባለመስማማታቸው ሊፈጸም ያልቻለ መሆኑን ሲገልፅ በሁለተኛ ተጠሪ በኩል ሥር ፍ/ቤት የቀረበው መልስ ለሚፈርሰው አጥርና ቤት እንዲሁም ለሚቀንስበት ይዞታ አመልካች ካሣ እንዲከፍሉ በአስተዳደሩ የተሰጠውን ውሣኔ ባለመፈፀማቸው አፈፃፀሙ እንዲታገድ መደረጉ በአግባቡ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1221 በተደነገገው መሠረት አመልካች /የሥር ከሣሽ/ በቂ መተላለፊያ ለማግኘት ለባለይዞታው ተገቢውን ማካካሻ መክፈል ሲገባቸው ይህንን ለመፈጸም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው መንገድ እንዲከፈትላቸው ማስገደድ አይችሉም በማለት የዳኝነት ጥያቄውን ውድቅ አድርጓል፡፡

የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እና የሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ ውሣኔ አፅንተዋል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ሲሆን የአመልካች ጠበቃ ጳጉሜ 2 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት አቤቱታ የመተላለፊያ መንገዱን አጠር ለማስገመት ለባለሙያ ሃምሣ ብር /50/ አመልካች መክፈላቸውን ገልፀው ከሁለተኛ ተጠሪ ይዞታ ላይ ለሚቀነሰው 1.10 ሜትር የአጥር ግምት ኪሣራ ለሁለተኛ ተጠሪ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆናቸውን ጠቅሶ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ተሽሮ ሁለተኛ ተጠሪ አጥር እንዲያፈርስ እንዲወስን ጠይቋል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ አመልካች የጉዳት ኪሣራ እከፍላለሁ እያሉ የመተላለፊያ መንገድ መከልከላቸው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ተጠሪዎች ባሉበት ለማጣራት ተጠሪዎችን አስቀርቧል፡፡ ነ/ፈጅ ስለአንደኛ ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች ሥር ፍ/ቤት ላይ

ማካካሻና የአጥር ግምት ለመክፈል ፈቃደኛ አልነበሩም ፍርድ ቤቶቹም ይህንኑ አረጋግጠዋል፤ በዚህ ሰበር ላይ የቀረበው አዲስ ክርክር ነው በማለት ኪሣራ ተወስኖ መዝገቡ እንዲዘጋ ጠይቋል ሁለተኛ ተጠሪ በበኩሉ የመተላለፊያ መንገድ ለመክፈት በአመልካች በኩል እንዲፈፀም የቀረበውን መፍትሄ ባለመፈፀም ግዴታቸውን ሳይወጡ ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ሲል ተከራክሯል፡፡

እኛም የግራቀኙን ክርክር እና ሕጉን በማገናዘብ መርምረናል፡፡ ከሥር ፍ/ቤት ውሣኔ መረዳት የተቻለው አመልካች መንገድ እንዲሰጣቸው ያቀረቡት ጥያቄ በአስተዳደሩ ተቀባይነት አግኝቶ በተጓዳኝ ደግሞ አመልካች ሊፈጽሙት የሚገባ ግዴታ በአስተዳደሩ በኩል የተወሰነ ስለመሆኑ ነው፡፡ በአስተዳደሩ የተወሰነው የኪሣራ ገንዘብ ለመክፈል አመልካች ፈቃደኛ መሆናቸውን በሰበር አቤቱታ የገለፁ ሲሆን በተጠሪዎች በኩል የቀረበው ክርክር አመልካች ፈቃደኛ እንዳልነበሩ በሥር ፍ/ቤት ተረጋግጧል የሚል ነው፡፡ በእርግጥም አመልካች በአስተዳደሩ የተወሰነውን ለመፈጸም ፈቃደኛ ያለመሆናቸው የሥር ፍ/ቤት በውሣኔው አረጋግጧል፡፡ አመልካች እዚህ ሰበር ችሎት ላይ ያቀረቡት ክርክር በፍሬ ነገር ረገድ ሥር ፍ/ቤት ያልተረጋገጠ በመሆኑ በዚህ ደረጃ ተቀባይነት የሚኖረው አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ግዴታቸውን ባልተወጡበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔን መቃወማቸው በሕጉ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘንም፡፡

የሥር ፍ/ቤት በውሣኔው በግልፅ ያመለከተው አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1221 መሠረት ተጠሪ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ተገቢውን ካሣ ሳይከፍሉ ተጠሪ መንገድ እንዲሰጣቸው ሊያስገድዱ እንደማይችሉ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው አመልካች በአስተዳደሩ የተወሰነው የመካካሻ ግዴታ ሳይወጡ ተጠሪን ማስገደድ አይችሉም የሚለው የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ሕጉን መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች የሚፈልግባቸው ተነፃፃሪ ግዴታ በአስተዳደሩ ውሣኔ መሠረት ከፈፀሙ በሕጉ መሠረት የመተላለፊያ መንገድ የማግኘት መብታቸው ወደፊትም ሊጠይቁ አይችሉም ተብሎ ውሣኔው የመጨረሻ ሊሆን አይገባም ምክንያቱም አመልካች እዚህ ሰበር ላይ እያቀረቡ ያለው ክርክር ካሣ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆናቸው እና በማንኛውም አካል ያለመጠየቃቸውን የሚያመለክት ሆኖ ስላገኘነው ነው፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ አሁን ባለበት ሁኔታ እንዲፀና ብለን ይህ ውሣኔ ግን የአመልካችን መብት እስከመጨረሻው የሚያሳጣ ሊሆን የሚገባ አይደለም ብለናል፡፡ በዚሁ መሠረት ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 03564 በ23/3/2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 09112 በ12/06/2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ የሰበር ችሎቱ በመ/ቁ 9816 የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በአስተዳደሩ ውሣኔ መሠረት ግዴታቸውን ከተወጡ በኃላ የመተላለፊያ መንገድ የማግኘት መብታቸውን ይህ ውሣኔ አይከለክልም ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

ም.አ

# ከውል ውጭ ኃላፊነት